AYNUMA (1)

(1)

t.me/BooksandYou

t.me/BooksandYou

(1)

AYNUMA (1)

### ዐይኑማ/ የማነሽ ዐይናማ

ደበሌ እጀታውና ክሳዱ መቆሸሸ የጀመረ የካኪ ካፖርት ለብሷል። በቀኝ ጆሮው ሕፅን ቀለሙ ሊያልቅ ትንሽ የቀረው፣ የላስቲክ ቱቦው ነጭ የሆነ ቀይ ቢክ ስክሪፕቶ ሰክቷል፡፡ አራት ማዕዘን ቅርፅ ብጣቂ ጨርቅ ከካፖርቱ ግራ የደረት ኪስ እፊያ ጠርዝ ላይ ተጣብቃለች። ስራ እያጣደፈው ወዲያ ወዲህ ሲል ወይም እቆመበት ሲነቃነቅ፣ ይህቺ ብጣሽ ጨርቅ ላይና ታች፣ ግራና ቀኝ እያለች በና ለመሄድ የምትከጅል ትመስላለች። ወደ ላይ ስትገለብ ***ሻገር ሆቴል*** የሚል መደብዘዝ በጀመረ ቀይ ማርከር የተፃፈ ፅሑፍ ይታያል። በግራ ክንዱ ብብት በስልት የተጠቀለለ የጋዜጣ ቱቦ ወሽቋል፡፡ እጆቹን ካፖርት ኪሶቹ ከቶ ከሁለት ሳምንታት በፊት ያጋጠመውን ነገር ያስባል……ይሄን ሲያስብ፣ አይኖቹ እንባ አቅርረው እንደ እርጥብ ብዮች መፍለቅ ጀመሩ……

❋

ሻገር ሆቴል ሁለት መግቢያዎች አሉት። አንደኛውና ዋናው ትልቁ መንገድ ጎን ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛውና ትንሹ ደሞ በጀርባ ነው። እዚህ ሆቴል ደበሌ አራት አመታት ሲሰራ ምናልባት እሱ ተረኛ ባልሆነበት ዕለት ካልሆነ በተቀር ለብቻዋ ያደረች ሴት፣ ለብቻው ያደረ ወንድ አጋጥሞት አያውቅም። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ዝዋይ ከተማ አጠናቆ በውጤቱ ዝቅተኛነት ዩንቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ሊገባ አልቻለም። ገንዘብም ስላልነበረው በግሉ ከፍሎ መማር አልሆነለትም። በዚህ ጭንቀት ውስጥ እያለ ረብሻ ይነሳና 'የሆነ የፖለቲካ ድርጅት ሊያሳስርህ እየፈለገህ ነው' ሲባል ጥቂት ቀናት እዛና እዚህ ሲንከራተትና ሲደበቅ ቆይቶ፣ አንደኛውኑ ወደ አዲስአባ ይመጣና በነሲብ በመረጠው *ደበሌ ተክሉ* በተባለ የውሸት ስም የቀበሌ መታወቂያ አወጣ። ለሆዱና ለልብሱ የሚሆን ትንሽ ገንዘብ ለማግኘት ሸገር ሆቴል ተቀጠረ። እስከዛሬ 'ይፈልግሃል' የተባለው ድርጅት አላገኘውም። ዛሬም እንደ ዝዋዩ ጊዜ በፍርሃት ባይሆንም አሳሪው ያለበትን ቦታ ደርሶበት እስኪወስደው ይጠብቃል።

እዚህ ሆቴል ተቀጥሮ ሲሰራ የተለያዩ ከባድና ቀላል አይነት ችግሮች አጋጥመውታል። ቀልዶችና አሳዛኝ ሁኔታዎች ታዝቧል። በሚያስቀው ስቋል። በሚያሳዝነውም አዝኗል። ከሶስት ሳምንታት በፊት ሚያዚያ መጨረሻ አካባቢ እንደሆነው አይነት ከስር መሰረቱ ያነጋው ሁኔታ በዚህች ምጥን ዕድሜው አጋጥሞት አያውቅም።

የሆነው በአጨሩ እንዲህ ነው……

ከምሽቱ አንድ ሰአት ላይ ዕድሜዋ በግምት 18 ወይም 19 የሚሆን ጥለቱ ቀይ ቀለም ያለው ነጠላ የተከናነበች ልጅ በጀርባ በር ገባችና ማከራያ ቢሮው ድረስ ቀጥ ብላ መጥታ ማረፊያ ክፍል እንደምትፈልግ ተናገረች። ደበሌ መልኳን እንኳን በደንብ ሳያጤነው (አለቃው ትጊ/ትዕግስት/ 'የሰው መልክ በተቻለህ መጠን ልብ ብለህ እይ' እንዳላለችው ሁሉ) ውብ ገፅዋ ላይ ማፍጠጡ በሌላ ነገር እንዳይተረጉምበት በማሰብ ብቻ፣ ካልተያዙት መኝታ ቤቶች እንዳመጣለት አምስት ቁጥርን መደበላት። እሷ ግን ሆቴሉን እንደምታውቀው ሁሉ 'ያንን ትሰጠኛለህ?' ብላ መታወቂያዋን በያዘ እጇ ወደ ሰባት ቁጥር አመለከተችው። ደበሌ በልቡ *በስራዬ ምን ከተታት* ብሎ በመገረም እያሰበ የጎሪጥ አያትና ክፍሉም ገና ያለተከራየ ሰለሆነ( 'የተከራየ ክፍል ነው' ብሎ ላይመድብላት ቢችልም) 'እሺ' አላት።

ስክሪፕቶ ከእሱ ተቀበለችና በመጀመሪያ ስም በሚጠቁመው አምድ ላይ *ዘውዲት ግርማ* ብላ ፃፈች። የቀሩትን ባዶ ረድፎች *ወረዳ------ቀበሌ------የቤት ቁጥር------*ብላ በተቀላጠፈ የእጅ ፅሑፍ መዝገቡ ውስጥ ሞላች። ስክሪፕቶውን በስርአት መለሰችለትና ልዩ ግብ እንደደረሰች ሁሉ ሳቅ ብላ አየችው (ማራኪ ፈገግታዋን ለራሱ ግልፅ ሊሆንለት ባልቻለ ምክንያት ልብ አላለውም)። መታወቂያዋ ላይ የሰፈረውን መረጃ ከፃፈችው መረጃ ጋር ከአመሳከረ በኋላ፣ ስምሙ መሆናቸውን አረጋግጦ መኝታ ቤቱን እንድታየው (ከሁኔታዋ ክፍሉን እንደምታውቀው ቢጠረጥርም፣ ጨዋ ለመሆን) በዝምታ አየመራ ወሰዳት። የሰባት ቁጥርን በር ከፍቶ እንድትገባ ጋበዛት። የተከራየችው

ክፍል ስትገባ፣ ከውጨ ቆሞ ሁኔታዋን እያየ ፈገግ ፈገግ፣ በልጠጥ በልጠጥ ቢልም፣ ለሰከንድ ሽራፊ እንኳን አይኖቿን ወደ እሱ ጣል አላደረገችም……

ፖሊስ ‘የተለየ ነገር ፊቷ ላይ ይነበብ ነበር?’ ወይ ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ የሚመልሰው አልነበረውም፡፡

የተከራየችው ክፍል እንደገባች (ጀርባዋን ለደበሌ ሰጥታ) ወደ አልጋው ሄዳ ገና ቁጭ ስትል፣ በሃይል ወደ ውጭ መተንፈስዋ ምን መረጃ ይሆናል? ጀርባዋን ወደ እሱ ስታዞር የሚያምሩ ባቶች፣ የሚያምር ጀርባ ነበራት ቢል ምኑ ለፖሊስ የሚጠቅም ኢንፎርሜሽን[1] ይሆናል? ደበሌን ዞር ብላም ሳታየው አልጋውን እየዳበሰች ‘ደህና ነው’ ስትለው የስንብት ሰላምታ እንኳን ሳይሰጣት በመጣበት ተመለሰ፡፡ (አሁን ሲያስብ *ምን ሊጠቅማት ነው ስለ አልጋው ምቹነት የተናገረችው?* ይላል)

ይሄን ከሌሎች ተከራዮችና እጃቸውን ሊታጠቡ ከሚመጡ የምግብ ቤቱ ተጠቃሚዎች፣ በሃረጎች የተከለለ ክፍል የመረጠችበት ምክንያት አላፊ አግዳሚ እንዳያያት፣ እሷንም ሆነ ወዳጇን ከወሬ ማሸሽዋ መሆኑን ጠረጠረ እንጂ ሌላ  ነገር አልመሰለውም፡፡ ለመከራየት ስትገባም የመጣችው በጀርባ በር ነው፡፡ የጀርባ በር መኖሩን ደሞ የሚያውቁት ብዙ ጊዜ ደጋጋሚ ተከራይ ደንበኞች ናቸው፡፡ አንዳንዴ አይነአፋር ሴቶች ወይም ከሰው አይን ለመደበቅ የፈለጉ ወንዶች ይመጡበታል፡፡ በጀርባ በኩል የመምጣትዋና ሰባት ቁጥር የመግባቷ ጉዳይ፣ አይነአፋር ለመሆኗ ምስክር የሚቆም መሰለው፡፡ እንዲህ ሲያስብ ግን ነቃ ብሎ አልነበረም፡፡ በዘልማድ ‘ሌሊት ተነስታ ልትሄድ ነው? ወዳጅዋ ገብቶ ጠብቂኝ ያላት ትሆናለች’ የመሳሰለ ነገር እያሰበ ነበር፡፡

ከግማሽ ሰአት በኋላ (ይሄንንም ልብ ያለውና ጠቃሚ መረጃ መሆኑን የተረዳው ፖሊስ ሲጠይቀው ነው) ከሆቴሉ ግቢ ወጣች፡፡ ግማሽ ሰአት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ጨርቅ የመሰለ ነገር የተሞላ በላዩ ላይ ምንም ፅሁፍ የሌለበት ልሙጥ ፌስታል ይዛ ተመለሰች፡፡ እሱ ያን ጊዜ ግቢው ውስጥ የድንጋይ መቀመጫ ላይ አረፍ ብሎ ካፖርት ኪሱ በደብተር ወረቀት ጠቅሎ ያስቀመጣትን ቁሩ ሲጋራ ለኩሶ እየጤሰ ነበር፡፡ ያየውና አትኩሮቱን የሳበው(ለፖሊሶቹ እንደተናገርው) አንጠልጥላ የያዘችው ፌስታል ነው፡፡ ከመሃል ‘ብቻሽን ነሽ?’ ብሎ ሊጠይቃት አስቦ፣ በአካባቢው የነበረው ጫጫታ፣ የልጅትዋ ችኩል የመሰለ አረማመድና ተከትሏት የሚጎተት የመሰለ እንግዳ ድባብ አገቱትና ሳያደርገው ቀረ፡፡ ይሄ የምትጎትተው ወይም ከቦ የሚከተላት ድባብ ከተሰራባቸው ነገሮች አንደኛው ውብ አይኖቿ እንደጉም የለበሱት ኮስታራነት ነበር፡፡ በጨለማ ሰበብ አልታየውም እንጂ፣ ይሄ ሰው የሚያሸሽ ድባብዋን ግትር ብሎ ከተዘረጋው፣ ካልተዝናናው ፌስታሉን ካልያዘው ግራ እጇ ማረጋገጥም ይችል ነበር፡፡ ግራ እጇ ግን በወዲያ በኩል ነው፡፡

እንደተለመደው እኩለ ሌሊት ላይ ከእሱ የሚጠበቅበትን ስራ ሁሉ አጠናቆ (የሆቴሉ በሮች በሙሉ መዘጋታቸውን ማረጋገጥ፣ ራት መብላት፣ ለመጨረሻ የሚያጤሰውን አንድ ሲጋራ መግዛት) ሊተኛ ሰራተኛ ክፍል ገባ፡፡ ልብሱን አወላልቆ፣ እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ አልጋ ውስጥ ጋደም ብሎ ሲያጤስ ጩኸት ሰማ፡፡

መጀመሪያ ድምፁ ከጓሮ በኩል የትጊ ወዳጅ ከነበረው አቶ ጅግሳ ከሚኖርበት የሆቴሉ ተጎራባቾች ከሚኖሩበት ድርድር ቤቶች ከአንዱ የመጣ መስሎት ነበር፡፡ በዛ በኩል ግን የዚያ አይነት ጩኸት ይቅርና ሰው ሲጠራራ ሰምቶ አያውቅም፡፡ ምናልባት ደሞ ከሴተኛ አዳሪዎቹ አንዷ፣ ከደንበኛዋ ወይም ከወዳጅዋ ጋር በልፊያ መሃል የምታሰማው ድምፅ መሰለው፡፡ ግን እንዲህ አንዴ ብቻ ከፍ ብሎ የሚሰማበትና ጩኸት የሚመስልበት ምክንያት ግልፅ አልሆነለትም፡፡ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ እንደገና የሆነውን በልቦናው ሲከልስ የድምፁ ልዩ የመሆን ነገር ከነከነው፡፡ ከእንግዳ ውበቱ ላይ ወፍራም መከራ የተለሰነበት ድምፅ ነው፡፡

የሲጋራው ቁሩ እንዳይበላሽበት ሲጋራውን በጥንቃቄ ተርኩሶ አልጋው ዳር እንደተቀመጠ፣ ያንን ጩኸት ዳግመኛ ለማዳመጥ ጠበቀ፡፡ ምክንያቱም የሰማው ድምፅ ውብና መከረኛ ብቻ ሳይሆን፣

---

[1] መረጃ

የሆነ የመቀጠል ተስፋ ያለው ይመስል ነበር። ለምን እንደሆነ አሁን ድረስ አይገባውም። ለሁለተኛ ጊዜ ድምፁ ቁልጭ ብሎ መጣ። ለሁለተኛ ጊዜ ድምፁን ሲሰማ አእምሮው ውስጥ የመጣችው ማታ ላይ ክፍል የተከራየችው ዘውዲት ነበረች። ድምፁን ለሁለተኛ ጊዜ ሲሰማ፣ ከማንም ከምንም ቀድማ በሃሳቡ የመጣችው ዘውዲት መሆንዋን ግን ለፖሊስ አልነገረም ('ለምን እሷ?' ቢሉትስ?)። ሱሪውን ሲያጠልቅ አንድ የስራ ጓደኛው በር በርግዶ ገባና፡

--ቁጥር ሰባት ያለችው ልጅ አንድ ነገር ሆናለች፣ አቦ ሌላ ሰው ደሞ ክፍልዋ አብሯት የለም አለው

ደበሌ ምንም ሳይናገር፣ የጫማዎቹን ሲር ሳያብት፣ ጓደኛውን ተከትሎት ወጣ። ዋናው ቤት መውጫና መግቢያ ላይ አለቃው ትጊ፣ ከእሁድ ዙረቷ መጥታ ገና ቦርሳዋን በትከሻዋ እንዳንጠለጠለች ቆማለች።

--ምን ሆናችሁ? ምን ጉድ ነው? እያለች አጠገብዋ ላለች አንድ ሰራተኛዋ ቦርሳዋን ስታቀብል፣ ደበሌ ምንም ሳይመልስላት ወደ ሰባት ቁጥር አቅጣጫ በችኮላ ሄደ።

የክፍሉ በር ገርበብ ብሏል። ከውስጥ ደብዛዛ ቢጫ መብራት ይወጣል። ከቤቱ ያረጀ የግድግዳ ቀለምና የአምፖሉ ደካማነት የመጣ እንደሆነ ያውቃል። ለትጊ ክፍሉን ቀለም እንድታስቀባ ነግሯት 'የእኛ ወንድ ቀዳዳ እንጂ ቀለም አያይም' ብላ አሹፋበታለች። በሩ ፊትለፊት እንደቆመ በመጣበት ፍጥነት መቀጠል እንደማይችል ገባው። በሃሳቡ የየልጅቷ ዐይኖችና የችኩል አካሄዷ ምስል ይመላለሳሉ። ወደ ኋላ ዞር ብሎ፡

--ማነው የጮኸው? አለ

--ቢቢ(ብርቱካን) ናት። በሩን ለብዙ ጊዜ ተገርብቦ ስታየው ገፋ አድርጋ ያየችውን አይታ በቃ ጮኸች (*እንዴት አላየሁትም በሩን?* እያለ ነበር በልቡ)

--የት ናት አሁን እሷ? ጮኻ ትጠፋለች? እያለ የሰባት ቁጥርን በር በቀስታ ገፋ አደረገና ወደ ውስጥ አየ። ትጊ ከጀርባው እየተንጠራራች ትገፋዋለች። የሽቶዋና የላብዋ ጠረን ተመሳጥሮ ይሰማዋል። በስተግራው ሁለት ሴቶችና ስለ ጩኸቱ የነገረው የስራ ጓደኛው ቆመዋል።

አንድ እርምጃ ተራምዶ ወደ ውስጥ ገብቶ ፊቱን ወደ ግራ እንዳዞረ፣ በድንጋጤ የተከፈተ አፉን በእጁ ከደነ። ይሄን ሁኔታውን ሲያዩ፣ ምን እንደሆነ ባይረዱም፣ የስራ ባልደረቦቹና ትጊ የማይታይ እጅ እንደገፋቸው ሁሉ ወደ ኋላ ወደ በረንዳው ጠርዝ አፈገፈጉ።

ዘውዲት አልጋው መሀል ደም የተነከረ አንሶላ ብርድልብስ ላይ ራቁቷን ተኝታለች። እጆቿ ግራና ቀኝ መስቀልኛ ተዘርግተዋል። ከአልጋው ስር እስከ በሩ ድረስ ጥቁር የደም ኩሬ ተኝቷል። በስተግራ ግድግዳው ላይ ደም ጠበልኛ ተረጭቷል (ዛሬ ድረስ ይሄ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ይጠይቃል። መልሱን አላገኘም)……

ደበሌ ይሄ ሲያጋጥመው የተነገረለት ድፍረቱ አብሮት አልነበረም። ተሳድቦ የሚያስከፍል፣ አስፈራርቶ የሚያሳምን፣ ተቆጥቶ የፈለገውን የሚያገኝ ደበሌ አልነበረም። ፊቱን መለስ አድርጎ አናቱን በሁለት እጆቹ ያዘ። እግሮቹ ክፍሉን እንደለቀቁ፣ በረንዳው ላይ ቆሞ ከአንድ ሰአት በፊት የበላውን መፅሐፈ ዶሮ ወደ ታች ወደ አትክልቱ መደብ አስታወከ። ማስመለሱ ታገስ ሲልለት እጁን ወደ ደረቱ ሰዶ የልቡን የጥንቸል ሩጫ ሲያዳምጥ ቆየ።

ትጊ ደበሌ ያየውንና የተረበሸበትን ነገር ላለማየት፣ እንደገባትና ሁሉን ነገር እንደምታውቅ ሁሉ እጆቿን እያራገበች፡

--በሉ……ዞር በሉ……ፖሊስ ልጥራበት……በሉ……ዞር በሉ……በሉ እንጂ……

እያለች ሰዎችን እየገፋች፣ እየነዳች ወደ ዋናው ቤት ሄደች። የደበሌ የስራ ጓደኛ ወንድ ነውና 'ከደበሌ የማላንስ ደፋር ነኝ' ለማለት፣ ከሴቶቹ ኋላ ቀርቶ ኮሰስ እያለ ወደ ክፍሉ በር ሲጠጋ፣ ደበሌ ዞር ብሎ፡

--ልትታመም ፈለክ? ተው ይቅርብህ አለው

ልጁ አልሰማም፡፡ ገና ፊቱን ወደ ውስጥ ብቅ ከማድረጉ በሁለት እጆቹም አናቱን ይዞ ተመለሰ፡፡

ደበሌ ፊቱን ከበሩ አዙሮ የሚያቃጥል መራራ ምራቅ እየተፋ ቆሟል፡፡ በድጋሚ የሚያስታውከው መስሎት ጎበጥ ብሎ ይጠብቃል፡፡ ትንሽ ሻል ሲለውና የሆዱ ነገር ሲያስተማምነው ጓደኛውን በረንዳ ላይ ትቶ ወደ ዘውዲት ክፍል ተመልሶ ገባ፡፡ አሁን ትዕይንቱ እንደ መጀመሪያው አልሰቀቀውም……

የግራ እጇዋ አምባር ማሰሪያ ላይ ቆዳዋ ሶስት ወይም አራት ሳንቲ ሜትር ያህል ተሸንትሮ መድረቅ በጀመረ ደም ተመርጓል፡፡ ገላዋ ከጡቶችዋ ጀምሮ እስከ ጉልበትዋ ደረስ የገረጣ ጠይም ነው፡፡ በስስ ፀጉር የተጋረደ የአፍረቷ ፍዝ ሽንትር ይታያል፡፡ አፏ በትንሹ ተከፍቶ የምትተነፍስ ትመስላለች፡፡ የሚያምሩ ዐይኖቿ ምንም ነገር ያልተሰቀለበትን ግድግዳ የሚያዩ ይመስላሉ፡፡ የሆነ ነገር ይመጣል ብላ የምትጠብቅም ትመስላለች፡፡ ከማሰሪያው የወጣ ፀጉሯ ከፊሉ በደም ላቁጧል፡፡ ደበሌ ባየው አልባሌ አለባበስዋ ስር የዚህ አይነት ማራኪ ገላ የያዘች አልመሰለውም፡፡ (እየቆየ የደነገጠው ደም በማየቱ ይሁን ወይ እንዳዛ የሚያምር ገላ በደም ተነክሮ ማየቱ ተምታቶበታል) ነጠላዋ በደም ተነካክቶ በከፊል ወንበር ላይ በከፊል ወለል ላይ ነው……አልጋው ራስጌ ካለው ጠረጴዛ ላይ ጥቁር የፕላስቲክ ማሰሪያ ያለው የኤሌክትሮኒክስ ሰአት ጀርባውን ወደ እሱ አድርጎ ተቀምጧል፡፡ ለሁለት የተሰበረ ባለ ሶስት ቀዳዳ ምላጭ ከሰአቱ ጎን ደም ለብሶ ተጋድሟል፡፡ ከእሱ ጎን የተጣጠፈ ሰፊ ብብት ያለው ወረቀት ተቀምጧል፡፡ ከእሱ ጎን ክዳኑ በቆቡ የገባ ቢክ ስክሪፕቶ አለ፡፡

--አላህ ነፍሷን ማራት፣ አላህ አድናት እያለ ፀሎት አጉተመተመ፡፡

ትጊ ባለተረከዝ ጫማዋን አውልቃ ባዶ እግርዋን ወደ ሰባት ቁጥር እየመጣች፡

--ብቻዋን ነበረች?

ደበሌ አልሰማትም፡፡

--አንቺ ብስብስ ስንቴ ልንገርሽ? ጫማዬን አምጪ፤ ደበሌ ጆሮህ ተደፍኗል? ብቻዋን ነበረች?

ከደበሌ ሁዋላ መጥታ ቆመችና ገና አይኖቿ ልጅትዋ ገላ ላይ ሲያርፉ፣ አፏን ከፍታ፣ አናቷን ይዛ የዘውዲትን ሁለመና ስታጠና ቆየችና ወደ በረንዳው ሸሸት አለች (ትዕይንቱን መድፈሯና እንደ እሱ አለመታመሟ ደበሌን እየገረመው)፡፡

--አዎ……እንጃ……የተከራየችው ለብቻዋ ነው አለ ደበሌ ትጊን ሳያይ……ከርሞ፡፡

--ፖሊስ ጠርቼለሁ፡፡ ምንም አትንካ፡፡ ምንም አትንኩ፡፡ በሩን ገርበብ አድርገው፡፡ በመያዣው አይደለም፡፡ ከላይ ከላይ ሳብ ብቻ አድርገው፤ አሻራ ይፈልጋሉ፤ አለች በባዶ እግሮቿ በረንዳ ላይ እየተንጎራደደች፡፡

እሷ እንዳለችው በሩን ገርበብ ሲያደርግ፡

--መብራቱን አጠፋህ? አለችው

--ይሁን ምንአለበት አለ በስጨት ብሎ

--ለአንተ ነው፡፡ ጎትተው ቢወስዱህ

--ቅድም ስገባ ስወጣ ነበር እኮ

--ቀልቃላ ሁሉ፡፡ አትንቀልቀሉ እላለሁ፣ የሚሰማኝ የለም

ደበሌ ደንገጥ አለ፡፡

--ልጅቷን ከዚህ ቀደም አይቼአታለሁ! አውቃታለሁ! አውቃታለሁ! ከዚህ በፊት ትመጣ ነበር፣ አንድ ሽበት ጣል ጣል ካደረገበት ሰውዬ ጋር፡፡ መቼ ዕለት ነው አንተ ሶዶ ደርሰህ የመጣኸው? ያኔ አከራይቼአታለሁ ትዝ ይለኛል አለች ትጊ፡፡

--ሶዶ አልሄድኩም፡፡ ዝዋይ ነው

--አዎ ዝዋይ፡፡ ቀኑ ትዝ ይልሃል?

--መጋቢት ሰባት

--አንተ የሄድክ ዕለት፡፡ የማልረሳበት ምክንያት በእድሜአቸው በጣም ያልተስተካከሉ ወንድና ሴት ስላየሁ ነው፡፡ ለምን ደብተሩን አናየውም?

--እርግጠኛ ነሽ?

--አዎ፡፡ ባልማርም አልዘነጋም

ወደ ኋላ ተመልሳ ሩብ ሰዓት አልወሰደባትም፡፡ ከወር በፊት የነበረ መዝገብ አምጥታ እያገላበጠች ስታይ ቆይታ፡

--እይ! እይ! ልክ ነኝ!

ደበሌ ተጠጋትና አንገቱን አሰግጎ አነበበ፡፡

--ዘውዲት ግርማ

--አየሀ አዳር ነው

--እንዴት ትዝ አለሽ? አለ ባድናቆት፡፡

--መጀመሪያ አይኖቿ፡፡ ከዛ እድሜዋ፡፡ አይኖቿ ይገርማሉ

ከደብተሩ ላይ እንዳነበበው ለደበሌ የበለጠ አስጨናቂ የሆነበት ከወር በፊት የተከራየችው ክፍል ሰባት ቁጥር መሆኑ ነው፡፡ ለትጊ ይሄን ገጠመኝ ሊያነሳላት ፈልጎ ባልገባው ምክንያት ዝም አለ፡፡

--ያውም ሰባት ቁጥር አለችው

አያት፡፡

--ምን ታየኛለህ? እዚህ ያለውን ነው የማነበው!

በሮ እንደሚያመልጣት ሁሉ ደብተሯን አቅፋ እንደያዘች፣ የመንቀረፈፍ ልማድ ያላቸው ፖሊሶች፣ የሚያፏጭ መኪናቸውን እየነዱ መጡ፡፡ ግማሽ ሰአት ያህል ዘግይቶ አምቡላንሱ ደረሰ፡፡

ከአንድ ሰአት ተኩል በኋላ ግቢው በለመደው የቀድሞው ፀጥታ ተጠቀለለ፡፡

ያን ቀን ሌሊት ደበሌ አልተኛም፡፡ ከበረንዳው ላይ መሄድ አልፈለገም፡፡ እዛና እዛ ይመላለሳል፡፡ እንዲህ የሚያምር ገላና ወጣትነት ዝም ብሎ ሲጠፋ መመሰከሩ ሊተረጉመው የማይችል ሚስጢር ሆነበት፡፡ ትዕግስት አንዳንዴ ከመሃል የመኝታ ቤቷን በር ከፍታ ሳትወጣ እያጮለቀች ታየዋለች፡፡ ለአራተኛ ጊዜ ስታየው (በሃሳቡ አራተኛ መሆኑን ቆጥሮ)

--ትጊዬ አትተኚም እንዴ፡፡ ደከመኝ ስትይ አልነበረም? አለ የተከዘ ፊቱን ሊደብቅ እየጣረ

--አንተ አትተኛም? አለችው ትጊ መልሳ፣ እንደ ቁጣ

ከሰራተኞቿ ሁሉ ትጊ እንደ ልጇ የምትወደው፣ እንደ ጓደኛ የምታዋራው ደበሌን ነው፡፡ ጨዋ መሆኑን ባልገባው መንገድ ፈትሻ(ሌባ መሆኑን፣ መዋሸቱን፣ ሚስጢር መጠበቁን ወዘተ) እሱ ሲኖር ብቻ ነው ተረጋግታ የምትሰራው፤ ወይም ቤቷን ትታ የትም የምትዞረው፡፡ ስታየው የሚያሳዝናትም ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ እንዴት እንደ ፈተሸችው እንደሰለለችው አያውቅም፡፡ አሁን በዚህ ባጋጠመው አደጋ ተረብሾ እንቅልፍ እንደማይወስደው ታውቃለች፡፡ የሴት ልብ ነው ያለው፡፡ ሩህሩህ ነው፡፡

--ደብዬ ና እስኪ አለችው

ሰምቶት አያውቅም ይሄን የድምፅዋን ቅላፄ:: ዞር ብሎ አያት:: አእምሮው ውስጥ የዘውዲት በደም የተነከረ አሪቅ አለ:: እነዛ የሚያምሩ አረንጓዴ አይኖች ያበራሉ:: አሁን ፀጉሩን በእንጨት ሚዶው ቢያበጥር የዘውዲትንም አብሮ የሚያበጥር ይመስለዋል::

ትጊ 'ና' አለችው በእናቷ ንቅናቄ:: በእጁ ይዞ የሚያንገላታቸውንና የሚጫወትባቸውን ቁልፎች ኪሱ ከቶ ወደ እሷ ሄደ::

--ምነው? አለችው በደከመ ድምፅ:: ተጠጋት:: (ጣቶቹ ካፖርት ኪሱ ውስጥ በቁልፉ ይጫወታሉ:: ከአልጋዋ ይዛው የመጣችው ሙቀት በቁመቱ ሙሉ ይሰማዋል)

--አይዞህ አለችው

--ያሳዝናል በጣም አለ

እጇን ትከሻው ላይ ጣል አድርጋ ወደ ደረቷ ሳበችው:: ደበሌ አንጎል ውስጥ የዘውዲት የሚያማምሩ አይኖች ቦግ ብለው የሚያፈሱት ፈገግታ ትዝ አለው:: በሞት የሚወሰዱ አይኖች አልነበሩም ......ውበት ዝም ብሎ እንዲህ የሚደረገም አይመስለውም ነበር፡፡ የትጊን ትከሻና መአዛ ተደግፎ ድምፁን ዝቅ አድርጎ መንሰቅሰቅ ጀመረ::

ትጊ ልጅ የላትም:: ልጅ ቢኖራት ደበሌ ቢሆን ትወዳለች:: ምክንያቱም ደበሌ ለዘውዲት እያለቀሰ ነው:: ለምን ዘግይቶ እንዳለቀሰ አልገባትም:: ጀርባውን እየዳበሰች ጥቂት ቆሙ:: መላከሞትን ያኮረፉ ከንፈሮቹን፣ መርጠብ የጀመሩ ጉንጮቹን፣ ብትስማቸው ትወዳለች:: ግን የእናት አልመሰላትም:: እሱን እንዳቀፈች ከርቀት የተዘጋውን ሰባት ቁጥር እያየች፣ በለሆሳስ ድምፅ:

--ደብዬ ተኛ፤ እንቅልፍ ጥሩ ነው አለችው

ከትከሻዋ ላይ ቀና ብሎ ራሱን ደፍቶ በዝምታ ወደ መኝታ ቤቱ ሄደ:: እሱ ክፍሉ ገብቶ በር ሲዘጋ በትጊ ጉንጮች ላይ መንታ የእንባ ዘለላዎች ወረዱ::

*

ከወር ተኩል በኋላ ጉዳዩን እንዲያጣራ የተመደበው ኮንስተብል ሻገር መጥቶ፣ ትጊና በዛን ቀን ተረኛ የነበሩ ሰራተኞች ተጠራርተው ክብ ሰርተው ይሄን አዳመጡት:

--በመጀመሪያ ምርመራውን ያቀለለልን ልጅቷ የሞተችበት አካባቢ ስላልተረበሸ ነው:: ማጅራቷ ላይ በፕላስተር የተጣበቀ ደብዳቤ አገኘን:: ለምን እዛ ላይ እንዳጣበቀችው አይገባንም:: እኛም እናንተም ባንጠነቀቅና ወረቀቱ ቢጠፋ ኖሮ፣ ተጠርጣሪ ትሆኑ ነበር:: በደብዳቤው ላይ ራሷን እንዳጠፋች ገልፃለች:: ሚጀ አርግዛ ወዳጇ እግርዝናዋን ስለካደ ራስዋን ለመግደል ወስናለች:: ወንድሞቼና እህቶቼ ያን ዕለት ሁለት ነፍስ ነው የጠፋው:: እንደዚህ አይነት አሰቃቂ ድርጊት በራሷ ላይ የፈፀመችው እዚሁ ወዳጅዋ ጋር የምታድርበት ሆቴል መጥታ ነው:: ሆቴሉ ብቻ ሳይሆን ያን ቀን የተከራየችውና ህይወቷን ያሳለፈችበት ሰባት ቁጥር ክፍል ከሰውዬው ጋር ደጋግመው ያርፉበት የነበረ ነው:: አላማዋ የእሷን ነፍስ ብቻ ሳይሆን ከፍቅረኛዋ ጋር ያሳለፈችውንም የደስታ ጊዜ፣ የደስታ ታሪክ ለማጥፋት ያቀደች ይመስላል:: (መፈላሰፍ ለፖሊስ ቤቱ ባይሆንም) ሰውዬው ተገኝቷል:: እሱን በሚመለከት ጥልቅ ምርመራ እየተካሄደ ነው (ስራችን የተጠናቀቀ የሚመስለው ይኖራል):: በነገራችን ላይ አስከሬን መርማሪዎቹ የገረማቸው የሚጀ አይኖች ቅጠልያና እጅግ ውብ መሆን ነው:: ታዝባችኋል?»

❋

ደበሌ የቀኑ ስራ አድክሞት አልጋው ላይ ሲያርፍና ገና ዕንቅልፍ ሲጥለው ማለም የሚጀምረው ዝዋይ ሐይቅንና ከሐይቁ ጋርም ገና ስምንት አመት ያልሞላት የአጎቱን ልጅ ነው፡፡ ጎፈሬዋን እያቦነነች ስትሮጥ......በተረከዞቿ የሚረጨው አሸዋ የሰሊጥ ጉም መስሎ ሁዋላ ሁዋላዋን ሲከተላት......በዋና የረጠበ ቀሚሷ ቀጫጫ ገላዋ ላይ የረጠበ አፎት መስሎ......ሁለመናዋ እንደ

ማግኔት ይስበዋል……ስለሚገዛላት ትንሽ ነገር ሲያስብ የገንዘብ ቦርሳው ቀዳዳ እንዳለው ትዝ ይለዋል፡፡ ደንግጦ የሚባንነው ይሄኔ ነው……

በእንቅልፍ ልቡ ምን ያህል ብር እንደቆጠበ ያስታውስና የምትፈልገውን ነገር ለመግዛት ምን ያህል ያስወጣው እንደሆነ ሂሳብ እየሰራ ከመሃል ዕንቅልፉ ተመልሶ መጥቶ ጠርጎ ይወስደዋል፡፡

የዘውዲትን አሟሟት ካየ በሁዋላ የሕልሙ መግቢያ ሁለመናዋ ደም በሚያንጠባጥንብ አይቷት በማያውቅ ልጃገረድ ተለወጠ፡፡ አንዳንዴ የአጎቱ ልጅ መስላው ሲያተኩር ሁለመናዋ ቀይ የሚያኸር ሴት ትሆንበታለች፡፡ አንዳንዴ ይህቺ በደም የተነከረች ሴት ፊት ለፊቱ ቆማ ጡቶቿን እያሸች፣ ምላሷን እያወጣች፣ ቀሚሷን እየገለበች በስድ የገላ ንቅናቄ ትሰድበዋለች:: ይኼ ቅዠት ስለተደጋገመበት በፀሎት ሊያስቀረው ቤተክርስቲያን መሄድ ጀመረ፡፡

--የት ነህ? ቹቹ ፈልጋህ ነበር ትለዋለች ትጊ

ቹቹ ወጣ ገባ እያለች ያስቸገረችው ሴት ጓደኛው ናት፡፡

--ቤተ ክርስቲያን፡፡ እደውልላታለሁ

--ከመቼ ወዲህ ቤተክርስቲያን ሂያጅ ሆንክ ደሞ?

--ያቺን ልጅ ካየሁ በሁዋላ…… ይላታል፣ ማንን ማለቱ እንደሆነ ይገባታል

--በል ቶሎ ና

--ቶሎ እመጣለሁ፤ ምን ይዤልሽ ልምጣ? አስጢፋኖስ ነው የምሄደው::

--በቃ የተመቸህን ያገኘሽውን  አምጣልኝ……ጧፍ ቢሆን ደስ ይለኛል:: ለቹቹ እነግራታለሁ::

ማንም ደጀሰላም እንዲሄድ ሃላፊነት እንዳላሸከመው፣ እንዳላስገደደው ያውቃል:: እስጢፋኖስ ሲሄድ ለራሱ ብቻ ሊፀልይ አልነበረም፡፡ ለማንም ባይናገረውም……የሚፀልየው፡

ለሚጢጢ ልጃገረዶች፣ ለሚጢጢ ብላቴናዎች በመንገድ ላይ  ለሚያያቸው፣ መሮጥ እንኳን ለማይችሉት……እየወደቁ ለሚነሱት……እየተነሱ ለሚወድቁት……መንገድ ዳር በሚያሳዝን አማርኛ ካሽ ለሚፈልጡት……ከእሱ ለሚያምሩት……በደፋሪዎች ጥላ ስር እንዲደፈሩ ለሚሰበኩት (አይዞሽ…… አይዞህ)

ለነፍሰጡር ወይዘሮዎች፣ አርግዘው ለሚንቀራፈፉት (ማርያም ትማራችሁ!)……

ለእናቱ፣ የት እንደደረሰች ለማትታወቀው(እዚህ ነኝ……እማማ እዚህ ነኝ)……

ለማያውቃቸው ሌሎች ሴቶች፣ የትም ላሉት (አይኖቻቸው ትላልቆች ቢሆኑም ባይሆኑም)……

ለመነኩሴዎቹ፣ ለእመምኔቷ፣ ለአቃቢቷ ለሌሎችም……

ለዘመዶቹ (ከነልጆቻቸው)፣ ሶዶ ዳሞት ላሉት ደሞ ዝዋይ ላሉት……

ለጠይም ውሃ እናቶች፣ ላሳዛኞቹ ባህሬይን የግፍ ባህር ለጠፉት (ሴት ቢሆን ኖሮ መሰደዱ አይቀርም ነበርና)……

ለሃበሻ ልጆች፡ ሚጥሚጣ ቀምሰው ለማያውቁ በየፈረንጁ አገር ላሉት (እዚህ ሆቴሉ በርበሬ ያልለመደ ምላሳቸው እየተለበለበ ሲያስለቅሳቸው……ይሄም የመጥፋት ምስልነት አለውና)……

ለትጊ ለራሷ (ብትቆጣውም……ባትቆጣውም)……

በግንባሩ የደጀሰላም ግድግዳ ተደግፎ ክፉ እንዳይደርስባቸው፣ እንዲያ እንዲያ ያለ በወጡበት የሚያስቀር ነገር እንዳያጋጥማቸው ያሰላስላል፡፡ በመጨረሻም ለራሷ ለማርያም፡ (ይሄን ሁሉ ተመልክታ ማልቀሷ ይቀራል? አይኖቿ በዕንባዋ ሳይታመሙ ይቀራሉ?)……

❋

……ደበሌ መንገድ ዳር ቆሞአል:: ነፋስ ሊቀበል ሲፈልግ ብዙ ጊዜ ከሆቴሉ ግቢ ወጣ ብሎ መንገድ ላይ አቧራ እየጠጣ ወሬ ያያል:: ማለት ንፁህ አየር ልሳብ ብሎ አቧራ ምን ያስምገዋል? ይሄ ልማዱ ትክክል ይሁን አይሁን ራሱን ጠይቆ አያውቅም:: ከሆቴሉ በስተቀኝ ወጣቶች እግር ኳስ ገጥመዋል:: እዚህ መንገድ ዳር ለምን እንደሚጫወቱ አይገባውም:: ቦታው 'ሜዳ ነው' ቢባልም የሜዳዎች አንዱም ፀባይ የለውም:: አባጣ ጎርባጣ፣ በኮረኮንችና በድቡሽት የተሞላ ነው:: ግራና ቀኝ መንገደኛ ይተላለፋል:: በስተቀኛቸው ትልቅ አስፋልት መንገድ አለ:: ይሄ በትክከል መጫወቻ ሜዳ አይደለም:: ከሆቴሉ መግቢያ ስር አንዳንዴ ትራፊ ምግብ 'የሚፈልጡት' 'አለቃ' አሉ:: ስማቸው 'አለቃ' ይሁን ወይ ቅፅላቸው ጠይቆ አያውቅም:: በረንዳ ላይ ልክ በዚህ ሰአት፣ ከዚህ መቀመጫ ላይ የማይጠፉ ጂግሳ የተባለ የትጊ ውሽማ ቡና አዞ ያዛጋል:: ቡና ቀርቦላቸው የሚያዛጉ ያስቁታል:: ግን አሁን መሳቅ አላሰኘውም:: የደንበኛ ጫጫታ ካደመቀው በረንዳ የይርጋ ዱባለና የማሪቱ ለገሰ አምባሰል ዘፈን እየተቆራረጠ ይመጣል፡ እኒህ አምባሰሎች አበሳል ያውቃሉ……ሳም ኦርጉ ይላሉ:: ብዙዎች ቢረሷትም፣ የዘውዲት ሁኔታ እስከአሁን ድረስ የደበሌን መንፈስ ረብሾታል:: በየቀኑ ሳያስታውሳትና ሳታስተክዘው አትቀርም:: በመጀመሪያ ያስደነገጠው የመኖርና የመሞት ቅርበታቸው ነበር (አጋጥሞት አያውቅም):: ሁለተኛ ደሞ የማያውቃት ልጅ ልክ እንደ አብሮ አደጉ የጠፋችበት ስለመሰለው ነው::

ወጣት ሆኖ ለወጣት በማዳላቱ ይሁን? ወይም እሱ ባይሞትም አንዳንዴ ለመገላገል ማሰቡና ይሄም ሃሳቡ በሚስጢር ከዛች ልጅ ጋር ሽርክ አድርጎት? ወይ የፍቅር ጥልቀቱ ግራ አጋብቶት? አንድ ሴት ሞተች ብሎ አምኖ ግን ቆይቶ ሁለት ነፍሳት መጥፋታቸውን መስማቱ? እርግጠኛ አይደለም:: የገባው አንድ ነገርና የፈራው ጠዋት ማታ ከአሟሟቷም ባይሆን ከልጅቷ ምውት ዛላ ፍቅር እንደያዘው ሁሉ መጠርጠሩ ነው:: እንዲህ አይነቱን ነገር ደሞ ለማንም ሊያወራ አይችልም:: የጤና አይደለም:: አንዳንዴ ለምን ልብሷን ለብሳ ራሷን እንዳላጠፋች ምክንያትዋን ሊገምት ይሞክራል:: ለምን? 'እንዲህ ወጣትና ያማርኩትን ልጅ የምትጥሉ' ብላ ልትነግር? ለማን? ለወዳጅዋ? ለተገኘው ተመልካች?

የካኪ ካፖርቱን ነፋስ እየገለበው ከሆቴሉ ውጭ ቆሞ 'አየር ሲቀበል'፣ የለቀስተኛ ሰልፍ በወዲያ በኩል ወደ ዮሴፍ በዘገምታ ሲያልፍ ያያል:: ሞተ በተባለው ሰው ምትክ እዛ ሬሳ ሳጥን ውስጥ ዘውዲት ያለች መሰለችው:: በሃሳቡ ሰባት ቁጥር ክፍል ውስጥ አልጋ ላይ እንዳያት በጀርባዋ ተኝታለች::

በራሱ እንደማፈር ብሎ በብብቱ የያዘውን ጋዜጣ አወጣና ትናንት ጠዋትና ማታ ያነበበውን አንድ ሪፖርት ለሶስተኛ ጊዜ ለማንበብ በቀስታ ገላለጠ፡፡ ገና ትኩስ ወሬ ነው፡፡ የዜናውን ሃያልነት ለመረዳት ደበሌ አይከብደውም፡፡ ግን ዘውዲ ከሞተች ጀምሮ ስለ ዘውዲ ሞትና አሟሟት የተፃፈላት ወሬ/ዜና እንዳለ ቢፈልግ፣ ነገ፣ ከነገወዲያ እያለ ቢጠብቅ አንድ መስመር እንኳን አልተፃፈላትም፡፡ አሁን የሚያነበው ዜና በስህተት እንደሞተ ተቆጥሮ መቃብር በመውረድ ላይ እያለ ከሞት ስለተነሳው ሚኒሊክ ስለሚባለው የሰፈሩ ሰው ነው፡፡ በዚህ ሰሞን ስለዚህ ተአምር የማያወራ ሰው በከተማዋ አለ ማለት ይከብዳል፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም ቢቢሲና ቪኦኤ ሁሉ መዝግበውታል ይላሉ፡፡ ብዙ ሰዎች በዚህ ዞግ[2] ስለ ፍካሬ ኢየሱስ መድረስ ያነበንባሉ፡፡ ሚኒሊክ አንዳንዴ ብቻውን እየመጣ የሚስተናገድ የሻገር ደምበኛ እንደ ነበር ትጊ ስታወራ ሰምቷታል፡፡ የጋዜጣው ሪፖርት በድጋሚ የሳበው የሆነ የቀረ፣ ማንም ሊረዳው ያልቻለ፣ ወይም በመጀመሪያ ንባቡ ያልደረሰበትን ትርጉም የሚያገኝ ስለመሰለው ነው፡፡ የመጀመሪያ ገፅ ላይ በስተግራ ጥግ ወዳለው አምድ አይኖቹን ወረወረ፡፡ የጋዜጣው ስም በትልቁ በማያምር ደብዛዛ ቀይ ቀለም ከወረቀቱ አናት ላይ አለ፡ *ገመና*:: እነዚህ ሶስት ሆሄዎች ዙርያ ጠመዝማዛ ሐረጎች ተስለዋል፡፡

---

[2] ሰበብ

ከሃረጎቹ መሃል ምን በመሆን ላይ እንዳለች ግልፅ ያልሆነ ቢጫ ፀሐይ ታበራለች፡፡ ጨረሮቿን የሚወክሉት እግሮች ብዛታቸው አስራ አራት ነው (ስራ ፈቶ እየቆጠረ)፡፡

## የሞተ ሰው ተነሳ ተባለ

ዘጋቢ

ፀሐይ ሙሉሰው

(ገዜአ) በነፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ ከሁለት ሳምንታት በፊት ስለተፈጠረው አንድ አስገራሚ ነገር የማያውቅ የመዲናችን ኗሪ ያለ አይመስለኝም፡፡ እስከአሁን በተለያዩ ፈርጆች ተመንዝሮና በነፋስ ስልክ ክፍለ ከተማና በጠቅላላ በሸገር ደምቆ እየተወራ፣ የቡና ማጣጪያችን ሆኖ እንደከረመ እናውቃለን፡፡ በተለያዩ ጊዜያት አንባቢዎቻችን የተስተካከለውን ዜና እንድናቀርብላቸው በደብዳቤና በስልክ ስለጠየቁን፣ በእኛ እምነት የመጨረሻውን ትክክለኛ መረጃ ልንሰጣችሁ ተነስተናል፡፡ ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ሃላፊነቱን ወስደን የማጣራቱን ስራ ሳንታክት ስንሰራ ቆይተናል፡፡ እኔና የስራ ባልደረቦቼ ያጋጠመን አንድ አስገራሚ ጉዳይ ትክክለኛውን መረጃ ከሚያውቁት ይልቅ፣ ከሰው ከሰው በቅብብል የሰሙት ራሳቸውን እንደ አዋቂ አድርገው በትምክህት ሲያወሩ ማድመጣችን ነው፡፡ ትክክለኛውን መረጃ ለአንባቢዎቻችን ማቅረብ የሙያ ግዴታችን ስለሆነ፣ በዚህ ተወዳጅ አምድ ላይ የምትጠብቁትን ያህል አትኩሮትና የሚታመን ግምገማ ለማድረግ ተነሳስቼአለሁ፡፡ በከተማችን መልካሙ ቢበዛም፣ የሚያሳዝኑን ጥቂት ነገሮችም ይፈፀማሉ፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት እዛው ሰፈር ውስጥ አንዷት ዕድሜዋ ሃያ ያልሞላ ወጣት የራሷን ሕይወት አጥፍታ የሁላችንንም ልብ በሃዘን አቁስላለች፡፡ ምንም እንኳዋን እንድትሞት የገፋፋት ጎልማሳ አርቲስት በፖሊስ ምርመራ ላይ ቢሆንም፣ ሃዘናችን አሁንም እንዳለ ነው፡፡ ይሄን ያደረገው ሰው ትክክለኛውን ፍርድ እንደሚያገኝ አንጠራጠርም፡፡ ጊዜው ፍትህ የነገሰበት ነው፡፡

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ ዘርዝረን ለማቅረብ ቃል በገባነው ጉዳይ ላይ እንዳተኩር ይፈቀድልኝ:: ይሄም ‘የሞተ ሰው ተነሳ’ ተብሎ ስለ yተሰራጨው አሉባልታ ላይ ዙም የሚያደርግ ነው፡፡

በመጀመሪያ ‘የሞተው ሰው ተነሳ’ የሚለው አረፍተነገር ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይኼ አባባል የሰውዬውን መሞት በፍፁም እንዳመነን ያመላክታል፡፡ መሆን የነበረበት ‘ሞተ የተባለው ሰው ተነሳ’ ነው፡፡ በቅርብ አውራ ጣት የሚያክል ሰው መሰል ፍጡር ነፋስ ስልክ አካባቢ ከውሾች ጋር ሲዞር አይተናል እያሉ ከሚያወሩ በጫት ከነበዙ ሰዎች አፍ ከምንሰማው ወሬ ጋር ተመሳሳይ ቅጥፈትነት አለው፡፡ በሃይማኖታችን ሙተው በክብር የሚነሱ እንደአሉ ይታመናል:: እንዲህ ሲሆን ውሉይ ሕይወት ይሉታል:: እኔ የማወራው ስለዚህ ውሉይ ሕይወት ስለተባለው አይደለም:: ምክንያቱም ሚኒሊክ አልሞቱም:: በድሮም ጊዜ ይሄው ውሉይ ሕይወት የሚሉት በተበላሸ ገንዛቤ ያልሞቱቱን ሞቱ እያሉ ይሆናል:: ወደ ሌላ ክርክር አልገባም:: በየትም የአለማችን ክፍል በችኩልነትና ባልተስተካከለ ምርመራ ‘ሞቱ’ እየተባለ ከተቀበሩ በሁዋላ የተነሱ ብዙ ሰዎች ናቸው፡፡ በሳይንስ የዚህ አይነት አሟሟት ኒር ዴዝ ኤክሲፒርየንስ (ኒዴኤ)[3] በእንግሊዘኛ NDE

---

[3] Near Death Experience (NDE)

ይባላል፡፡ ይሄን የመሰሉ በታሪክ የተመዘገቡ ብዙ ተመሳሳይ ገጠመኞች ማቅረብ ይቻላል፡፡ እውቁ የቀልድ ልብወለዶችና ታሪክ ፀሐፊ ጳውሎስ ኞኞ ይሄን ሁኔታ በሚመለከት ጥቂት አስደናቂ ታሪኮች መዝግቧል፡፡ አውራጣት የሚያክል ሰው አለ ብሎ የሚያምን፣ የሞተ ሰው ተነሳ ብሎ ማውራት ይቸግረዋል አልልም፡፡

አቶ ሚኒሊክ በሰፈሩ ታዋቂ ግለሰብ የሆኑት በጥረታቸውና በፈጠራ ችሎታቸው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሃብት አፍርተው ገንዘባቸውን ወገን መጥቀሚያ በማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በዚህች አገራችን ፍትህ እንዲሰፍን በነፋስ ስልክ፣ በጎተራና በጎፋ አካባቢ ፋሺሽታዊውን ደርግ መግቢያ መውጫ ያሳጡ፣ በአገራቸው ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ የታገሉና ያታገሉ፣ በባዕድ አገር ተሰደው እየተሰቃዩ ከመኖር ይልቅ፣ እዚሁ ከወገናቸው ጋር ደጉንም ክፉውንም አብረው ለማሳለፍ የወሰኑ ታላቅ ሰው ስለ ነበሩ ነው፡፡ እሳቸውን የማያውቅ የነፋስ ስልክ ኑዋሪ የለም፡፡ ከታወቁ ባለሃብቶች ጀምሮ፣ በቅፅል ስሙ 'አለቃ' ተብሎ እስከሚጠራው የሻገር ሆቴል ተስፈኛ ድረስ ሁሉም የእሱን ስም ባድናቆት ያነሳሉ፡፡ አቶ ሚኒሊክ ከሞት ቢነሱልን ሁላችንም ደስተኞች እንሆን ነበር፡፡ ግን ለዚህ አልታደልንም፡፡ የከተማዋው ዝነኛ አልቃሽ ነርስ ንጋት ወንድምዋ እንደሞተባት ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እያለቀሰች ስታስለቅስ ልብ ትነካ ነበር፡፡ እንዲህ ያለ ልዩ ግጥም እንዴት ሊመጣላት እንደቻለ ስንጠይቃት፣ ከአይኖቿ እንባ እየፈሰሰ መናገር ተስኗት ነበር፡፡ ወንዶችንና ሴቶችን ያብረከረከ ግጥምዋን የገጠመችው የመስዋዕትነቱ ተካፋይ የነበሩ ሰዎች እውነተኛ ታሪኩን ስለነገሯትና መንፈሷን ስለቀሰቀሰው እንደሆነ ነግራኛለች። በሰፈሩ ኗሪ መሆን የጀመርኩት በቅርብ ቢሆንም፣ የአቶ ሚኒሊክን ዝናና ገድላቸውን ከተማኝ ሰዎች ስለሰማሁ አድናቂያቸው ነበርኩ፡፡ ለብዙ ወጣቶችም አርአያ እንደነበሩ የሚያውቁአቸው አበክረው ይናገራሉ፡፡ የአገሪቷ ብርቅዬ ልጆች ቁጥራቸው እየመነመነ ሲሄድ ማየት ከምንም የበለጠ ያሳዝነኛል፡ ፡ እኔም (ከሃዘኔ እየታገልኩ) ማስታወሻዬ ላይ ካሰፈርኳቸው አንዳንድ ግጥሞቿ ላቃምሳችሁና አብራችሁ የሃዘኑ ተካፋይ ይሁኑ፡፡

*ወንድ ወደቀ ዛሬ በዚህች አደባባይ*

*ሚኒሊክ የሚባል የወንዶች የበላይ፡፡*

*ወታደር አልገዛው አልተሰበር ቅስሙ*

*ቅዱስ ሚኒሊክ ነው ካሁን ወዲያ ስሙ፡፡*

*አገሬ ኡኡ በይ አሁን ፈላ ጉዱ*

*ደርግን ያራወጠው ትቶን ሄደ ወንዱ፡፡*

*ፋሺስት ፋሺስት ብሎ ልክ እየነገረ*

*ወደ ማንቀርበት መቃብር በረረ፡፡*

*ጎምለል ጎምለል የሚል ክንፋም ነው አሞራ*

*ሰማነው እገነት ጓዶቹን ሲጣራ፡፡*

ከአስራ አምስት ቀናት በፊት አርብ ዕለት ከሰአት በሁዋላ አቶ 'ሚኒሊክ ባዩ' የነፋስ ስልክ አካባቢ የተከበሩ ኗሪ አርፈዋል ተብሎ ሬሳቸው በስርዓት በቤተሰቦቻቸው፣ በጎረቤቶቻቸው፣ በወዳጆቻቸው፣ በእድረተኞችና በዘመድ አዝማድ ታጅቦ ወደ ጴጥሮስ ጳውሎስ መካነ መቃብር ይገባል፡፡ የአቶ ሚኒሊክ ሳጥን መቃብሩ ወርዶ ገና አፈር መመለስ ሲጀመር፣ ለቀስተኞች ጩኸት ሰማን፡፡ እኔ እንደ አንድ ሰፈረተኛና የዕድር አባል መቃብሩ ጠርዝ ነበርኩ፡፡

t.me/BooksandYou

መቃብሩ ጋ የሆነው በዝርዝር እንዲህ ነው፡፡ ሳጥኑ በከፊል አፈር እንደለበሰ ከሳጥኑ ድምፅ ተሰማ፡፡ በእርግጥ እንግዳ ነገር ነውና መቃብሩ ዙርያ የነበረነው ሁሉ ተደናገጥን፡፡ ያው ተደናግጠን አልቀረም በመረጋጋት አቶ ሚኒሊክን አፈር ከለበሱበት ለማውጣት ርብርብ ጀመርን፡፡ የተቀበሩበትን ሳጥን የምንክፍትበት መሳሪያ ብዙም ሳንንገላታ ቅርብ ካለ ገራዥ አገኘን፡፡ አገራችን የሃይማኖት አገር ናት፡፡ የሳምራዊት፣ የሼክ ሁሴንና የተክለሃይማኖት አገር ናት፡፡ ታምራትን ለምደናል፡፡ የአቶ ሚኒሊክ ባለቤት ዙፋን ሳጥኑ ቤቱ ሂዶ እንዲከፈት ስለተለማመነች፣ አየር እንዲያገኝ ተደርጎ በመጣበት መኪና ተጭኖ ወደ መኖሪያው ሄደ፡፡ የሚኒሊክ የቅርብ ወዳጆቹ ብቻ ቤቱ ሲገቡ፣ የቀረነው ተመለስን፡፡ ሳጥኑም እንደ ቤተሰቦቹ ፍላጎት እዛው መኖሪያው ቤቱ በስርአት ተከፈተ፡፡

ከፖሊስና ከሐኪሞች በሰማነው ሪፖርት መሰረት አቶ ሚኒሊክ በጠና በመታመማቸው የሞቱ መሰሉ እንጂ አልሞቱም፡፡ ከላይ እንደ ጠቀስኩት በሳይንስ ኒር ዴዝ ኤክስፒሪየንስ ይባላል፡፡ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1975 አም ራይሞንድ ሙዲ የተባለ ሰው ከሕይወት በሁዋላ ሕይወት(life after Life) በተባለው መፅሐፉ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ትንታኔ አድርጓል፡፡ ነገረ ጉዳዩ አሳሳቢ በመሆኑም በ1981 በአለም አቀፍ ደረጃ የኒር ዴዝ ኤክሲፒሪየንስ ጥናት ተቋም ተመስርቷል (International association of Near Death studies)፡፡ በአሜሪካን አገር እስከስምንት ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች ይሄን በሚመስል ጉዳኛ ልምድ ውስጥ አልፈዋል ይባላል፡፡ NDE በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ችግር እንደሆነ ሳይንቲስቶችቹ ይናገራሉ፡፡ ይህ ማለት አንድ ሰው በተለያዩ መለኪያዎች ሞተ የሚያሰኙትን ነገሮች ያሙዋላና በዘመናዊ መሳሪያ ብቻ ሊመዘገብ/ቡ ወይም ሊነበብ/ቡ የሚችል/ሉ ረቂቅ ሰበብ/ሰበቦች ሳይደረስባቸው ይቀራሉ፡፡ ለምሳሌ በስሜት ሕዋሳቶቻችንና በመሳሪያ ልንመዘግበው በማንችል መልክ ልብ ትመታለች፣ ግን ሞተ ተብሎ ይወሰንና በሽተኛው/ዋ ይቀበራል/ትቀበራለች፡፡

ከሐኪም ሪፖርትና ከቤተሰቡ በደረሰን ሪፖርት መሰረት ሚኒሊክ የጠና የስኳር በሽታ ነበረበት፡፡ ለሕይወቱ ያሰጋዋል እየተባለ ሞቱ ይጠበቅ ነበር፡፡ የሰራ አካላቱ ሲፈዝና መናገር ሲያቅተው፣ ብዙ የማያውቁ ዘመዶቹ ሞቷል ብለው ገንዘው በሳጥን ይከቱታል፡፡

ከዚህ የምንማረው ፍሬነገር አለ፡፡ አንድ ሰው መሞቱን ለማረጋገጥ በእንግሊዘኛ ‘ኦቶፕሲ’ (autopsy) የሚባለው በሰለጠነ ሰው መደረግ እንደ አለበት ነው፡፡

ይሄ የሚያሳየን፣ በችኮላና በትዕግስት የለሽነት፡

1/የሰውዬው ሳጥን ሲከፈት የሰራ አካላቱ ጠፍቶ ጭንቀላቱ ብቻ ተገኘ፣ በዚህም ሚስቱ ገድላዋለች ወይም አስገድላዋለች ብሎ ማውራትና ማስወራት፣

2/እንዲህ በመሆኑም ቤተሰቦቹና ወዳጆቹ በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተጠርጥረው በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንደዋሉ ማውራትና ማስወራት፣

3/ሟቹ ምንነቱ ባልታወቀ ልዩ በሽታ እንደታመመና መንግስት ይሄን ሚስጢር አድርጎ እንደደበቀው ማውራትና ማስወራት፣

4/አሜሪካን በሚገኝ አንድ ኢንሹራንስ ካምፓኒ እህቱ በእሱ ስም የሕይወት ኢንሹራንስ ስለገባች፣ አቶ ሚኒሊክ ቢሞቱ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ዶላር እንድታገኝ ተብሎ የውሸቱን እንዲሞት ገፋፍታው የተደረገ ሲሆን ነገር

**ግን ሚኒሊክ ገና መቃብር ሲገባ በመፍራቱ፣ ሴራው እንደተባላሸ ሲያወሩና ሲያስወሩ፣ እኛ እውነቱን አዋቂዎች በማዘን አዳምጠናል፡፡**

**አሉባልታው በዚህ አላበቃም፡፡ ቤቱ ከተመለሰ በሁዋላ አቶ ሚኒሊክ ሲያለቅስ እንደሰሙ የአካባቢው ሰዎችና ጎረቤቶቹ ሲናገሩ ነበር፡፡ ይሄን በሚመለከት ባለቤታቸውን ወይዘሮ ዙፋንንና አብሮ አደግ የትግል ወዳጃቸውን አቶ እስጢፋኖስን ለማነጋገር እድል አጋጥሞን ነበር፡፡**

**<u>ወይዘሮ ዙፋን</u>፡ 'ሚኒሊክ ልጆቹን ይወዳል፡፡ ያለ እነሱ አይሆንለትም፡፡ በልጅነቱ ጎበዝ ተማሪ ስለነበር ልጆቹ እንደ እሱ እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የተሻሉ እንዲሆኑ ጠዋት ማታ ይለፋል፡፡ ከእነሱ ሊለይ በመሆኑ ነው ያለቀሰው'**

**<u>አቶ አለማየሁ</u>፡ 'ምን ይታወቃል? እሱ ቢናገረው ይሻል ነበር፡፡ ሚኒሊክ እንደ ባሕር የሰፋ ልምድ ያለው ሰው ነው፡፡ ጠቅላላ ባሕሩ ይሁን ወይ ከዛ ጨልፎ ባስታወሰው ትንሽ ነገር፣ ብቻ በዚህ ሰበብ አለቀሰ ማለት ብንችልም፣ በሙሉ ልባችን ግን መናገር ይከብደናል፡፡ በወጣትነቱ ጊዜ ደርግ ባደረሰበት ስቃይ ህሊናው እንደ ቆሰለ ነው፡፡ ያ ከላይ እስከ ታች አንድን ትውልድ የመተረ ዘግናኝ ዘመን አሁን ድረስ የሚያቃዠን ብዙ ነን፡፡ የደስታ ለቅሶ እንዳልሆነ ግን ይገባኛል'**

**ምንም እንኳ ጎረቤቶቹ ማልቀሱን ቢሰሙም፣ የቀረቡላቸውን ምክንያቶች የማያምኑ አጋጥመውናል፡፡ ሙታንን በማንገላታትና ሃዘንተኛን በመረበሽ፣ በአሉባልታ ግፊት ፍተሻ እንዲደረግ የሚገፋፉ፣ ጉዳዩ እንዲጣራ የሚጠይቁ አሉ፡፡ ይሄ ትክክል ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ አይደለም……**

ደበሌ ጋዜጣውን ጨርሶ ሳያነብ አጣጠፈና እንደሚያስብ ሁሉ ባዶ አየር ላይ አተኮረ፡፡ እዚህ ላይ የተፃፈውን ሁሉ ማመን አልቻለም፡፡ ያደከመው ነገር ደሞ ፍልስፍናና እንግሊዘኛ ለባብሶ የሚመጣ መከራከሪያ ነው፡፡ በቀላሉ የገባው ጉዳይ ግን ሚኒሊክ የተባለው ሰው ከዘውዲት የበለጠ ተሰሚ እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱን ማሰብ ይፈልጋል፡፡ ምስኪን አልጋ አንጣፊ ነውና፣ የትም እንደማይደርስ ስለሚያውቀው ደሞ ማሰብ አይፈልግም፡፡ ለቃላት ለቃላት ስለዘውዲት ሲያስብ ጭንቅላቱ ውስጥ ደጋግሞ የሚመጣው 'ንፅሕት' የተባለ ቃል ነው፡፡ እንደዛ በደም ተጨማልቃ፣ ከማንኛውም አይነት መንፈሳዊ ወይም ስጋዊ ስርአት ውጭ የራሷን ሕይወት አጥፍታም ቢሆን ሲያስባት አሁንም አእምሮው ውስጥ የቀረው ንፅሕት የመሆኗ ግምቱ ነው፡፡ *በእርግጥ ራሷን ገላለች? ራሷን እንድትገድል ሌላ ካመቻቸትስ? ቤሳ የገዛችበት ገንዘብ የማነው? አልጋ አላከራየሁዋትም?*

ከስንት አመታት ጀምሮ የተከማቸው ማንም የሰበሰበው ጣጣ የእሱም ትንሽ ነገር ተጨምሮ ልጅቷ ላይ አርፎ የደፈጠጣት መሰለው፡፡

ከጀርባ፣ ከሆቴሉ ግቢ የሚያውቀው የቹቹ ማርመላታ ድምፅ ይጠራዋል(የማይጣፍጠው ማነው?)

--ደበልዬ! ዴቢ!

የስሙ መጠራት አነቃውና ዞር አለ:: አይኖቹን ለአፍታ መለስ ሲያደርግ ከእሱ ብዙ ሳይርቅ አንድ ነጭና ጥቁር ቀለም ያለው የጫማ ማሰሪያ አየ:: አራት እርምጃ ያህል ተራመደና አነሳው:: ማሰሪያው ብቻውን ሊሆን አይችልም ብሎ በመገመት መንታውን ፍለጋ እዛው አካባቢ በአይኖቹ መማተር ቀጠለ::

--ደበልዬ ! ዴቢ !

በወፍ እንደሚጠራ ነው::

የቼቼ ፀባይ ሙሉ በሙሉ ተመችቶት አያውቅም፡፡ የደበሌ ችግር በሁሉ ነገር ውስጥ ፍቅር የመፈለግ ነው፡፡ ስለፍቅር የመፈረም ነው:: የሚበላውን ሲያካፍል ካንጀቱ ነው፡፡ የሚጠጣውን ሲያካፍል ከኩላሊቱ ነው፡፡ የሰጡትን ሲቀበል በልቡ የፍቅር እንዲሆን ተመኝቶ ነው፡፡ በዚህ በዚህ ብልቶቹ (ነርቮቹና ልቡ) ስራ እንደበዛባቸው ትዝ አይለውም::

ሆቴሉ በሰው ከሞላ ቼቼ ሁልጊዜ ሻገር የምትገባው በጀርባ ነው፡፡ ቼቼ ለግላጋ ገላ ስር የሚረማመደው ደመነፍስ ሳይሆን ብልጠትና ፍቅር ነው፡፡ ከነዚህ ከመንታዎቹ አንዱን አንጥራ ማውጣት ከብዷታል:: ከሁለት ሳምንታት ወዲህ ደበሌ ቼቼ ገላ ላይ ተነቃንቆ፣ የሚደርስበት ደርሶ፣ በጀርባው ሲገለበጥ፣ እሷ ከአልጋ ተነስታ፣ ውስጥ ሱሪዋን እየለበሰች ያላወለቀችውን አጭር ቀሚሷን ወደ ታች ስትጎትት......ከተንጋለለበት አይኖቹን ጨፍኖ ወይም በውስጥ ሱሪ አልጋ ደርዝ ላይ ተቀምጦ ......መሬት ላይ እዛና እዛ የወደቀ የሶፍት ፔፐር ቁርጥራጮች፣ ዘሩን የሰበሰበ ጎማ እያየ ለምን ባዶነት እንደተሰማው ለራሱ ማሰብ ጀምሯል......

.....እና አሁን ቼቼ ስትጠራው ሰምቷታል ደሞ አልሰማትም፡፡ እጅግ በፍጥነት የዘነጋት ይመስላል::

ዞር ሲል ልብ ያለው ነገር በአይኖቹ ሙሉ ዕንባ መከተሩ ነው፡፡ ከላይ አስከታች በቁመቱ ሙሉ በሚፋጅ ዕንባ የተሞላ መሰለው:: ፊቱን ከእሷ ዞር አድርጎ፣ ዕንባው በነፋስ እስኪደርቅ ጥሪዋን ሳይመልስላት ቆሞ ጠበቃት::

--ደህና አይደለህም? አለችው ከጀርባው አቅፋው:: እንደተደበረ ከአቋቋመሙና ከገፁ ስርአት ገብቷት:

--ደህና ነኝ

ግራና ቀኝ አይታ......ደሞ ወደ ጀርባዋ አይታ......ማጅራቱ ላይ ስርቆሽ ሳመችው:: ዞር ብሎ የሚንቀራፈፍ እጁን ወገቧ ላይ አስቀመጠ:: ቀይ ቢላቢሎ ቀሚሷ እንደ ጉም ዙሪዋን እየተርገበገበች፣ የሰሊጥ ብጥብጥ የመሰሉ ጭኖቿ ጠቅላላ ነፋስ ስልክ ላይ አስማታቸውን እየቀለሙ......

--ትጊን ጠየኩሁዋት እሁድ እረፍት ትሰትሃለች:: በሚያፌዝ ኮልታፋ አንደበት::

ይሄን ብላው ፈገግ እያለች እሱ ብቻ እንዲሰማ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ክፍሉ እንዲሄዱ ጠየቀችው::

--ብዙ ስራ አለብኝ፣ ለምን የማይሆን ጊዜ ብሎ አይኖቿን አተኩሮ አያቸው:: ካፖርቱ ደረት ኪስ ላይ ባለችው ጨርቅ እየተጫወተች:

--ተገብክ አሁንስ፡፡ አንድ ሚስትር አሳይሃለሁ አለችው እየሳቀች::

ቼቼ ለአልጋ ብቻ አይደለም የተፈጠረችው (ቁሌታሞች እንደሚሉት) ፣ እንደቀረፋ እንጨት ተሰባብራ ሻይ፣ ቡናና ወጥ የምትሆን ናት፡፡ የቼቼን ገላ ማንም እምቢ አይልም፡፡ የነካው ካልሆነ፡፡ ቼቼ ከደበሌ ከፍ አድርጋ የምትወደው ገንዘብ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ያለ ገንዘብ ሕይወት የለም፡፡ ለሚቀርቧት እንደምትለው ሀብት ቢኖራት ከደበሌ አትለይም፡፡ ገንዘብ ከሚሰጧት ጋር ስትተኛ በልቧ ሁልጊዜ ደበሌ ነው......አጠገቧ ደሞ ከሌለ ልክ እሱ መዋደድን እንዳበላሽ ሁሉ ጎርበጥባጣ ውስጥዋ ላይ ቅናት ይዘንባል፡፡ እጁን እየጎተተችው፣ እሱም እየተጎተተ ወደ መኝታ ቤቱ ገቡ:: በሩን መለሰችና:

--ሹፍ የያSኩትን ለማንም እንዳትናገል

--ምን?

አይኖቹን ወደ ታች ወረወረ፡፡

የትንሽ ቦርሳዋን ዚፕ ከፈት አድርጋ በሰልፍ የተደረደሩ መአት መቶ ብሮች አሳየችው፡፡

--ከየት አገኘሽው?

--መአት ሺህ ነው፣ ለማንም እንዳትነግል፡፡ ለትጊም ቢሆን፡፡ ለእማማ ነግላ ታስነትከቀኛለች፡፡ እገልሃለሁ። በአመልካች ጣቷ ጉሮሮውን ገዘገዘች፡፡ እጇን ይዞ የገዘገዘችበትን ጣቷን ለብቻው ነከሰው።

--እንዴ! አሳመምከኝ ዴቢዬ!

-- የት አገኘሽው?

--መንገድ ላይ ማታ በፌስታል ወድቆ

--በፌስታል? አለ በጥርጣሪ

--ሶለን ትሙት አታምነኝም። ምንድነው ብዬ በእግሬ ነካ ነካ አደለኩት። በካ በላስቲክ መአት ታስሎ ታስሎ......ሰካራም የታለው መሰለኝ.....

የመጨረሻውን አረፍተነገር ስትናገር አንገቷን ሰበረች። ማልቀስ የምትፈልግ መሰለችው። ውሸቷን እንደሆነ ይገባዋል። የአንገቷን አሰባበር፣ የፀጉሯን ጆሮዋ ላይ አወዳደቅ፣ ደሞ በጣቶቿ ገለል አደራረጓ ተጠራጣሪነቱን አሸነፈው። እንደምትወደውም ያውቃል፣ ብትቀባዥርም፡፡ ገና ሲነካት ነው ከውስጧ ማካፋት የምትጀምረው።

አልጋ ደርዝ ተቀመጠችና እንዳስጠላት ሁሉ ገንዘብ የያዘ ቦርሳዋን ወደ ጎን ወረወረችው። ቀና ብላ አየችው። ዐይኖቿ ይፈልቃሉ። ከንፈሮቿን ነክሳለች። እንዲህ ስትሆን ቆሞ በዝምታ ሊያያት አልፈለገም። ጎንዋ ተቀመጠና አቀፋት። የካኪ ካፖርቱ የወጥ፣ የአንሶላ፣ የብርድልብስ፣ የላብ ጠረን ቢሸትም ቺቺ ግድ አልነበራትም። ፊቷን ዘንበል አደረገችና የበላት ነገር እንዳለ ሁሉ ጉነጨዋን በትከሻው አከከች። ከአገጨዋ ቀና አድርጎ በሊፕስቲክ የቀላ አፏን ሳመው። ከተቀመጡበት ተያይዘው አልጋው ላይ ተንጋለሉ።

--እውነቴን ነው አለችው

--እሺ አለ በግድየለሽነት

--በእማማ ሞት እመነኝ

--አምንሻለሁ። የሚያስከፋትን ሊናገር አልፈለገም። እንደሚያስብ ያስታውቃል።

አንገቱን አቅፋ ይዛ አንጋጣ አየችው፡፡

--ሁሌ ትናፍከኛለህ። በሰአት በደኪካ ምናምን አይ ሴዌል[4]። ኮልታፈነቷ ላይ ኮልታፋነት ሲጨመር ሁሌ ምን እንደምትፈልግ ያውቃል......

--ደበልዬ......ማልዬ ማልነት......ማልሻ......ማሉ......እወድሻለሁ በለኝ (በጆሮው)

በከፊል ይሰማታል......ደሞ በከፊል አይሰማትም......ለሀብቷ አልነበረም ደበሌ ደረቷ መሃል ያረፈው......ቀይ ቀሚሷ ወደ ላይ በቀርፋፋ ስልት እየተሳበች......የቡናማ አይኖቿ ስፋት ውስጥ በረሃ ያያል......ከስሩ እንደ እባብ ናት......አንገቷ በወዝ ይፈልቃል......ፊቱን እዛ ቀብሮ አብሯት ይነቃነቃል......እውስጡ የተሰበሰበውን የዕንባ ዶፍ እንደ ወጨፎ ሊጥለው ይለፋል......በእሷ ዜማ እየታጀበ......ደሞ የተከፈለ ልቡን ያዳምጣል......እንደተሰናኙ ቢገባውም ያልተሰናኙም ይመስለዋል። በሲዖ ስሜት። አንዱ ሲዖ ዘውዲት ጋ ነው። የቀረው ሲዖ ምን እንደሆነ አያውቅም።

--ማልዬ......ማ......ሉ የእኔ ማል......ደበልዬ......እወድሻለሁ በለኝ(ወደ ኮርኒሱ አንጋጣ)። በቅርብ የተላመጠ የማስቲካ ጠረን የተዘባረቀበት ፊቱ ላይ ይነፍሳል።

---

[4] እምላለሁ